# በምርጫ ሕግ ውስጥ የድምፅ መብት ድንጋጌዎች አካታችነትን በተመለከተ የተዘጋጀ አጭር ሀተታ

ፀሀፊ፡ ዮሀንስ ታከለ

ይህ ህትመት በኢትዮጵያ የህግ ባለሙያ አካል ጉዳተኞች ማህበር ከኦፐን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ ጋር በመተባበር የተዘጋጀ ነው። በሰነዱ የተገለጸ ይዘት እና ሀሳብ/አመለካከት በማንኛውም መንገድ የኦፐን ሶሳይቲ ኢኒሼቲቭ ፎር ኢስተርን አፍሪካ አመለካከትን አያንጸባርቅም።

ሐምሌ 7, 2014

## Contents


1. እንደ መግቢያ ........ 1

2. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት አንቀጽ 29 በወፍ በረር ........ 2

3. የምርጫ ሕጉ አካታችነት ሲፈተሽ ........ 5

4. እንደ ማጠቃለያ ........ 11

## 1. እንደ መግቢያ

ዜጎች የአንዲት ሉዓላዊት ሀገር ባለቤት መሆናቸውን ከሚያረጋግጡባቸው መብቶች አንዱ ድምጽ የመስጠት መብት ነው። በተለይ በምዕራባውያን ዘንድ ድምጽ የመስጠት መብት ከቁንጮ የሰባዊ መብቶች መካከል አንዱ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ እንግዲህ ከዴሞክራሲ ስርዐታቸው ማደግ ጋር ተያይዞ ድምጽ የመስጠት መብት ወሳኝነት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ እየሆነ በመምጣቱ ነው።

ድምጽ የመስጠት መብት ለመጀመሪያ ጊዜ ዓለም አቀፋዊ እውቅና ሊያገኝ የቻለው በዓለም አቀፉ የሰባዊ መብቶች መግለጫ አማካኝነት ነው። ይሄው መግለጫ በተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባኤ በ1948 ሲጸድቅ ካካተታቸው ሰባዊ መብቶች መካከል አንዱ ድምጽ የመስጠት መብት ነበር። ድምጽ የመስጠት መብት ሁነኛ የዜጎች ሰባዊ መብት ስለ መሆኑ በአንቀጽ 21 ላይ ተደንግጎ እናገኘዋለን።

ይሁንና ይሄው መግለጫ ድምጽ የመስጠት መብት እና አፈጻጸሙ ከአካል ጉዳተኞች አንጻር ምን ሊመስል እንደሚገባ ያለው ነገር የለም። እንዲያውም መግለጫው አካል ጉዳተኛውን ማኅበረሰብ አያውቀውም። እርግጥ ነው ስለ ጤና እና ተያያዥ ጉዳዮች በሚደነግግበት አንቀጹ አካል ጉዳት (disability) የሚል ቃል ተካትቶ እናገኛለን። ሆኖም በአንቀጽ 25 አካል ጉዳት (disability) የሚለው ቃል የተካተተው አካል ጉዳተኛ የተሰኘውን ማኅበረሰብ ሳይሆን እንደ ሕመም፣ ሥራ አጥነት፣ እርጅና፣ ወዘተ የመሳሰሉ ሁኔታዎችን (event) ለመግለጽ ነው።

መግለጫው ከወጣ ከ18 ዓመታት በኋላ በጠቅላላ ጉባኤው የጸደቀው ዓለም አቀፉ የሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን በአንቀጽ 25 የድምጽ መብትን በሰባዊ መብቶች መግለጫ ከተቀመጠው ሰፋ በማድረግ አካትቶት እናገኛለን። ለምሳሌ እንደ ድምጽ መስጠት ባሉ የፖለቲካ ተሳትፎ የእኩል እድል ተጠቃሚነት መርሕን (principle of equal opportunity) ያስተዋወቀው ይሄው ቃል ኪዳን ነው።

ሆኖም ይሄው ቃል ኪዳን ልክ እንደ ሰባዊ መብቶች መግለጫ ሁሉ ድምጽ የመስጠት መብትን ከአካል ጉዳተኞች ልዩ ሁኔታ አንጻር አልተመለከተውም። እንዲያውም ይባስ ብሎ በአንቀጽ 25 መሰረት ድምጽ የመስጠት መብት ከሚከለከልባቸው ምክንያቶች መካከል አእምሮአዊ አካል ጉዳት (mental disability) አንዱ እንደ ሆነ በቃል ኪዳኑ ጠቅላላ አስተያየት (General Comment) 25 ላይ አስቀምጧል። ቃል ኪዳኑን የመተርጎም ሀላፊነት የተሰጠው የሰብአዊ መብቶች ኮሚቴ (Human Rights Committee) በቃል ኪዳኑ ጠቅላላ አስተያየት (General Comments) 25 ላይ እንደ ገለጸው ከሆነ አእምሮአዊ የአካል ጉዳት ያለባቸው ዜጎች ድምጽ የመስጠት መብታቸውን እንዲያጡ ቢደረግ ሕጋዊ እና ምክንያታዊ ነው። እንደኮሚቴው አተረጓጎም ከሆነ በዓለማችን ላይ ካሉ አካል ጉዳተኞች መካከል በብዛት ትልቁን ድርሻ የሚወስዱት አእምሮአዊ አካል ጉዳት ያለባቸው ወገኖች ሁሉ ድምጽ የመስጠት መብት የላቸውም።

ከአካል ጉዳተኞች ሰብአዊ መብቶች አንጻር በእነዚህ እና በሌሎች ዋና ዋና የሰብአዊ መብቶች ሰነዶች የታየውን ክፍተት ለመሙላት ለሀያ አንደኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ ስምምነት (Convention) ሆኖ የወጣው የተባበሩት መንግሥታት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት በ2006 በጠቅላላ ጉባኤው ጸድቆ በ2008 ሥራ ላይ ውሏል። ይሄን ስምምነት በማጽደቅ እና የሕጎቿ አካል በማድረግ ሐገራችን ኢትዮጵያ ከመጀመሪያዎቹ ተርታ ትሰለፋለች። ስምምነቱ ከአካተታቸው

በርካታ መብቶች አንዱ ድምጽ የመስጠት መብት ነው። ድምጽ የመስጠት መብት የአካል ጉዳተኞች የፖለቲካ ተሳትፎ ከሚገለጽባቸው መብቶች አንዱ ስለ መሆኑ በአንቀጽ 29 ተደንግጎ እናገኘዋለን።

ከዚህ በታች በሚኖረን የመጀመሪያ ክፍል የአካል ጉዳተኞች ድምጽ የመስጠት መብትን ከስምምነቱ አኳያ በአጭሩ እንመለከታለን። ስምምነቱ ሰብአዊ መብቶችን ከአካል ጉዳተኞች ልዩ ሁኔታ አንጻር በድጋሜ ከማካተቱ ባሻገር የአካል ጉዳተኞችን መብቶች በተመለከተ ለሚወጡ ሀገር በቀል ሕጎች ዓለም አቀፍ ዝቅተኛ ሰብአዊ መብቶች ደረጃ (minimum standard) ሆኖ ያገለግላል። ስለ ሆነም  በምርጫ ሕጎችን ውስጥ የተቀረጹ እና ከመምረጥ እና ከመመረጥ ጋር የተያያዙ ድንጋጌዎችን ከስምምነቱ አንጻር በሁለተኛው ክፍል በአጭሩ እንገመግማቸዋለን።

## 2. የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት አንቀጽ 29 በወፍ በረር

ከዓለማችንን ሕዝብ ውስጥ ሩብ የሚሆነውን የያዙት አካል ጉዳተኞች እስከ ቅርብ ጊዜ በነበረው እና አሁን ድረስ በብዙ መልኩ ተንሰራፍቶ በሚገኘው የተደራሽነት መሰናክል ድምጽ በመስጠት በፖለቲካ መሳተፍን ጨምሮ የተለያዩ ሰባዊ መብቶችን  ለመጠቀም እንዳይችሉ ተደርገው ኖረዋል። የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት በአካል ጉዳተኞች መብቶች ላይ ለሚፈጠረው  ሁለንተናዊ መሰናክል ምላሽ ይሆን ዘንድ የጸደቀ ስምምነት ነው።

ስምምነቱ ሁሉንም አካል ጉዳተኞች የሚሸፍን ብቸኛው እና አስገዳጅ ስምምነት እንደ መሆኑ አካል ጉዳተኞች በአካል ጉዳታቸው ምክንያት የሚፈጸምባቸውን የትኛውንም መድሎ እና መገለል ይከለክላል። አካል ጉዳተኞች በአካል ጉዳታቸው ሳይገለሉ እና መድሎ ሳይፈጸምባቸው የፖለቲካ መብቶቻቸውን ጨምሮ ማንኛውንም ሰብአዊ መብት ከጉዳት አልባው ማኅበረሰብ እኩል እንዲጠቀሙ ይደነግጋል። በተለይ አንቀጽ 29 አካል ጉዳተኞች ድምጽ ከመስጠት፣ እጩ ከመሆን እና ከመሳሰሉት የፖለቲካ ተሳትፎ ዐይነቶች ጋር ተያይዞ የሚገጥማቸውን የተደራሽነት መሰናክል ለመቅረፍ በማሰብ የተደነገገ አንቀጽ ነው። የአንቀጹ ይዘት እንደሚከተለው ሊጠቃለል ይችላል።

1. አካል ጉዳተኞች በሕዝብ እና በፖለቲካ ጉዳዮች የመሳተፍ መብት አላቸው። እንዲሁም የመምረጥ እና የመመረጥ መብታቸው  የተጠበቀ ነው። ለዚህ መብት አፈጻጸም
   - i. የድምጽ አሰጣጥ ስርዓቶች፣ መገልገያዎች እና ቁሳቁሶች ተገቢ፣ ግልጽ እንዲሁም ለመረዳት እና ለመጠቀም ቀላል መሆን አለባቸው።
   - ii. አካል ጉዳተኞች በምርጫዎችና ሕዝበ ውሳኔዎች ወቅት በሚስጥር ድምፃቸውን የመስጠት፣ በምርጫ የመወዳደር . . . አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ድጋፍ ሰጪ እና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን የመጠቀም መብት አላቸው።
   - iii. በመራጭነታቸው አካል ጉዳተኞች ፍላጎታቸውን በነፃነት የመግለጽ እና በድምጽ መስጫ ወቅት እራሳቸው በመረጡት ሰው ድጋፍ የመቀበል መብታቸው መጠበቅ ይኖርበታል።

   ለ. አካል ጉዳተኞች ሕዝባዊ ጉዳዮች በሚከናወኑበት ወቅት ያለምንም አድሎ ከሌሎች ጋር በእኩልነት መሳተፍ የሚያስችል አካባቢ ሊፈጠርላቸው ይገባል። በተጨማሪም

I. የሀገሪቱ ህዝባዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች በሚመለከቷቸው መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራት እና በፖለቲካ ፓርቲዎች እንቅስቃሴ እና አስተዳደራዊ ሥራ ውስጥ አካል ጉዳተኞች እንዲሳተፉ ማድረግ ይገባል።

II. በዓለም አቀፍ፣ በአህጉር አቀፍ፣ በሀገር አቀፍ፣ በክልል እና በአካባቢ አካል ጉዳተኞችን የሚወክሉ ማኅበራት እንዲፈጠሩ ሁኔታዎች ሊመቻቹ ይገባል።

አንቀጽ 29 በአንድ በኩል ራሱን ችሎ ፣ በሌላ በኩል ከአንቀጽ 3 (ጠቅላላ መርሖች) ፣ ከአንቀጽ 4 (የተዋዋይ መንግሥታት ጠቅላላ ግዴታዎች) ፣ ከአንቀጽ 5 (እኩልነት እና መድሎን አለመፈጸም) ፣ እንዲሁም ከአንቀጽ 9 (ተደራሽነት) ጋር ተናቦ ይተረጎማል። በሕግ ፊት እኩል እውቅናን ስለማግኘት የሚደነግገው አንቀጽ 12 ከ1 እስከ 9 ካሉ ድንጋጌዎች መካከል ባለመገኘቱ በአቀራረጽ የመርሕ ወይም የጠቅላላ ድንጋጌ ቁመና የለውም። ይሁንና በአንቀጹ የተካተተው መብት ሰፊ እና ለብዙ መብቶች መፈጸም መሰረት በመሆኑ በአንቀጽ 29 ለተቀመጠው የመምረጥ እና የመመረጥ መብት እውን መሆን በአንቀጽ 3, 4፣ 5 እና 9 እንደተቀመጡት ጠቅላላ ድንጋጌዎች ዐይነተኛ ሚና ይጫወታል።

አንቀጽ 12 አካል ጉዳተኞች በሕግ ፊት ከሌላው ጋር እኩል ስለ መሆናቸው፣ በሰውነታቸው ሕጋዊ ችሎታ እንደ አላቸው እና በችሎታቸውም ሕጋዊ ውጤት ያላቸውን ተግባራት እንደሚከውኑ ይደነግጋል። በሌላ በኩል ድምጽ መስጠት ሕጋዊ ውጤትን ከሚያስከትሉ ተግባራት አንዱ በመሆኑ ውጤታማነቱ በዚህ አንቀጽ ላይ የተመረኮዘ ይሆናል። ስምምነቱ ከሲቪል እና የፖለቲካ መብቶች ቃል ኪዳን በተለየ መልኩ አንድ አካል ጉዳተኛ በሕግ ፊት እንደ ሰው እውቅና የማግኘት መብቱ የሚገፈፍበትን ወይም የመምረጥ መብቱ ሊገደብ ወይም ሊነፈግ የሚችልበትን ልዩ ሁኔታ አላስቀመጠም።በሌላ አገላለጽ አንቀጽ 12 እና አንቀጽ 29 ተጣምረው ሲተረጎሙ አእምሮአዊ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ወገኖች ጨምሮ አካል ጉዳተኞች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ከሌላው ጋር እኩል የመምረጥ እና የመመረጥ መብት ይኖራቸዋል። የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ኮሚቴ አንድ ሰው አእምሮአዊ የአካል ጉዳት ያለበት መሆኑ በምንም መልኩ በአንቀጽ 29 የተመለከተውን የመምረጥ መብት እንደማያሳጣው በጠቅላላ አስተያየት (General Comment) 1 እና በኮሚዩኒኬሽን 4/2011 በድጋሚ አረጋግጧል። ኮሚቴውም ሆነ ሕጉ በአንቀጽ 29 የተቀመጠውን የመምረጥ መብት የትኛውንም የአካል ጉዳት መሰረት በማድረግ ለመገደብ ወይም ለመከልከል የሚያስችል ሕጋዊ መሰረት እንደሌለ ቢያሳዩም በአለማችን ከሚገኙ ሀገራት መካከል 80% የሚሆኑት አእምሮአዊ የአካል ጉዳትን መሰረት በማድረግ የመምረጥ መብትን አሁን ድረስ በተለያየ መጠን ይገድባሉ ወይም ይከለክላሉ።

አንቀፅ 29 ተዋዋይ መንግሥታት አካል ጉዳተኞች በፖለቲካ እና በሌሎች የሕዝብ ጉዳዮች በንቃት መሳተፍ የሚችሉበትን ስርዓት እንዲዘረጉ እና ድምጽ የመስጠት መብታቸውን ከሌላው እኩል መጠቀም ስለ መቻላቸው እንዲያረጋግጡ ይደነግጋል። በአንቀጽ 3 የተደነገጉት እና ግላዊ ምርጫ የማድረግ ነፃነት (personal autonomy)፣ መድሎ አለማድረግ እና አለማግለል (non-discrimination)፣ አካታችነት (inclusion) እና ተሳትፎ (participation) የሚሉት ጠቅላላ መርሖች አካል ጉዳተኞች በአንቀጽ 29 የተካተቱ መብቶችን በሚጠቀሙበት ወቅት አንዳች መድሎ እና መገለል እንዳይደርስባቸው ተጨማሪ ክልከላ የሚያደርጉ መርሖች ናቸው። በአንቀጽ 4 (3) መሰረት ስምምነቱን ተግባራዊ ለማድረግ በሚወጡ ሕጎች ወይም ፖሊሲዎች ዝግጅት እና አፈፃፀም፣ ወይም አካል ጉዳተኞችን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በሚኖሩ የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውስጥ ተዋዋይ መንግስታት አካል ጉዳተኞችን በንቃት እንዲያሳትፉ ጠቅላላ ግዴታን ተቀምጧል። ይህ ድንጋጌ

በአንድ በኩል በዋነኝነት ስምምነቱ ከመጽደቁ በፊት በነበረው ዓለም አቀፍ የአካል ጉዳተኛ መብቶች ንቅናቄ ወቅት ከፍ ብሎ ይስተጋባ የነበረው ያለእኛ ለእኛ (nothing for us without us) የሚለው መፈክር ነጸብራቅ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ አካል ጉዳተኞችን በትክክል ያካተቱ ሕጎችና ፖሊሲዎች እንዲፈጠሩ የአካል ጉዳተኞች የኑሮ ልምድ እውቀት (experiential knowledge) ትልቅ ግብአት መሆኑን ያመለክታል። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ቢያንስ አካታችነትን በሚመለከት የምርጫ ሕጎቻችን እና የአፈጻጸም ደንቦቻቸው፣ የመራጭ አመዘጋገብ እና የድምጽ አሰጣጥ ስርዐቶች በአካል ጉዳተኞች ተሳትፎ ተፈትሸው ያለፉ መሆን ይኖርባቸዋል።

አካል ጉዳትን መሰረት ያደረገ መድሎን እና ማግለልን የሚከለክለው አንቀጽ 5 ደግሞ አካል ጉዳተኞች ድምጽ የመስጠት መብትን ጨምሮ ማንኛውም ሰብአዊ መብቶቻቸውን ሲጠቀሙ በተዋዋይ መንግሥታት በኩል አስፈላጊው ማመቻቸት (accommodation) እንዲደረግላቸው ይደነግጋል። ለምሳሌ በአንቀጽ 29 ላይ በተቀመጠው መሰረት አንድ አካል ጉዳተኛ ከአካል ጉዳቱ የተነሳ ድምጽ ለመስጠት የትኛውም እክል ቢገጥመው የድምጽ መስጠት ማመቻቸት (voting accommodation) እንዲቀርብለት ስምምነቱ ያስገድዳል። ለእያንዳንዱ ድምጽ ሰጪ አካል ጉዳተኛ ከሚደረግለት የተመጣጠነ ማመቻቸት ባሻገር አካል ጉዳተኞች ድምጽ የመስጠት መብትን ከመጠቀማቸው በፊት መንግሥታት ቀዳሚ የተደራሽነት እርምጃዎችን እንዲወስዱ በአንቀጽ 9 መሰረት ይገደዳሉ። በመሰረቱ አንቀጽ 29 በተለይ ከአንቀጽ 9 ጋር ተቆራኝቶ ሊነበብ እንደሚገባ ልብ ይሏል። በሌላ አገላለጽ ለአንድ ድምጽ ሰጪ አካል ጉዳተኛ የተመጣጠነ ማመቻቸት የሚቀርብለት በአንቀጽ 9 መሰረት አስቀድሞ የተወሰደው የተደራሽነት እርምጃ የድምጽ ሰጪውን ችግር ለመፍታት በቂ ሆኖ ካልተገኘ ብቻ ነው። አንድ ተዋዋይ መንግሥት በድምጽ መስጫ ቀን ለእያንዳንዱ አካል ጉዳተኛ ድምጽ ሰጪ የተመጣጠነ ማመቻቸት ስለማደርግ በአንቀጽ 9 በተደነገገው መሰረት አስቀድሞ የምርጫ ጣቢያዎችን፣ የድምጽ መስጫ ማሽኖችን፣ ምርጫ ነክ መረጃዎችን፣ ወዘተ ተደራሽ ማድረግ አይጠበቅብኝም ሊል አይችልም።

ከአንቀጽ 29 ጋር አንቀጽ 9 በይዘቱ ሰፊ እንደ መሆኑ የሚወሰዱት የተደራሽነት እርምጃዎች ከአካላዊ (physical) እስከ ተግባቦታዊ (communicational), ከመረጃ (informational) እስከ ሕግ ማሻሻል (legal) እርምጃዎች ሊደርሱ ይችላሉ። ለምሳሌ ተዋዋይ መንግሥታት ማንኛውም አካል ጉዳተኛ እንደ እድሜ እና ዜግነት የመሳሰሉ በሕግ ተቀባይነት ያላቸው መስፈርቶችን እስካሟላ ድረስ የመምረጥ መብቱን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ መጠቀም እንዲችል ሕግ ነክ መሰናክሎችን ማስወገድ አለባቸው። ምርጫ ነክ መልእክቶች፣ የምርጫ ዘመቻዎች፣ የፓርቲ ሰነዶች፣ የድምጽ መስጫ ወረቀቶች እና ሌሎችም ለዓይነ ስውራን እና ለሌሎች ሕትመት የማንበብ ውሱንነት (print disability) ላለባቸው መራጮች በተደራሽ ፎርማት እንዲዘጋጁ፣ ድምጽ የሚሰጠው በማሽን ከሆነ ማሽኑ ተደራሽ እንዲሆን፣ ማንኛውም አካል ጉዳተኛ ድምጽ በሚሰጥበት ወቅት ሚስጥራዊነቱ እንዲጠበቅ ወዘተ ማድረግም የመንግሥታቱ ግዴታዎች ናቸው። የምርጫ ጣቢያዎች መገኛቸው ብቻ ሳይሆን የጣቢያዎቹ በሮች እና የውስጥ ክፍሎች፣ በተለይም መራጭ ብቻውን ሆኖ በሚስጥር ድምጹን የሚሰጥበት ክፍል (polling booth) እና የመጸፊያ ጠረጴዛው ተሽከርካሪ ወንበር ለሚጠቀሙ መራጮች ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይጠበቅባቸዋል። መስማት የተሳናቸው መራጮች የፖሊሲ አማራጮችን አውቀው መምረጥ እንዲችሉ የምርጫ መልእክቶች፣ የፓርቲ ሰነዶች፣ የምርጫ ዘመቻዎች፣ ወዘተ በምልክት ቋንቋ እንዲዘጋጁ እንዲሁም በመራጭ ምዝገባ እና በድምጽ መስጫ ወቅት የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ እንዲኖር የሚያስችል ስርዐት መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል። ማንኛውም አካል ጉዳተኛ መራጭ በመራጮች ምዝገባ ወይም በድምጽ መስጫ ቀን አስፈላጊ ሆኖ ከታየው በመረጠው ረዳት ድጋፍ እንዲያገኝ በሕግ ከመቅረጽ ጀምሮ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። እንዲሁም የአካል

ጉዳት እና ክብደቱ የተለያየ ከመሆኑ ባሻገር የምርጫ ጣቢያዎችን መቶ በመቶ ተደራሽ ለማድረግ በተግባር የማይሳካ በመሆኑ በውክልና ድምጽ የመስጠት መብትን ጨምሮ አማራጭ የድምጽ መስጫ ስልቶችን መንደፍ ሌላው ግዴታ ሆኖ ይተረጎማል፡፡

አካል ጉዳተኞች በሲቪል ማኅበራት እና በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ በአባልነት እና በአመራር እንዲሳተፉ ማድረግ ሌላው ስምምነቱ የሚያስቀምጠው ግዴታ ነው፡፡ የዚህ ግዴታ ዓላማ ከመምረጥ ባሻገር አካል ጉዳተኞች የመመረጥ እና የመወከል እድል እንዲያገኙ ለማስቻል ነው፡፡ በብዙ ሀገራት አካል ጉዳተኞች የመምረጥ መብታቸው ከሞላ ጎደል ቢጠበቅላቸውም የገላጭ ውክልና (Descriptive Representation) መብት ግን ተነፍጓቸው ይገኛል፡፡ ከጥቂት የአፍሪካ ሀገራት በስተቀር የአካል ጉዳተኞችን የገላጭ ውክልና መብት በሕግ የደነገገ ሀገር እስከ አሁን አልተገኘም፡፡

በቀጣዩ ክፍል ደግሞ የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግን አካታችነት ከስምምነቱ አንጻር በአጭሩ እንመለከታለን፡፡

## 3. የምርጫ ሕጉ አካታችነት ሲፈተሽ

የኢፌድሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 38/1/ "ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት....... ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥ . . . እና የመመረጥ መብት እንዳለው ይደነግጋል፡፡ በሌላ በኩል ሕገ መንግሥቱ በአንቀጽ 54 (2 እና 3) የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች ጋር በአብላጫ ድምፅ የምርጫ ሥርዓት እንደሚመረጡ እና አናሳ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከ20 ያላነሰ መቀመጫ እንደሚያገኙ ደንግጎ ይገኛል፡፡

በእነዚህ እና በሌሎች የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች የተገለጹ ተያያዥ መብቶች ወደ መሬት እንዲወርዱ ግን ዝርዝር ሕግ ያስፈልጋል፡፡ "የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጅ ቁጥር 1162/2019" ዝርዝር ሕግ ሆኖ መውጣቱ ለዚሁ ዓላማ ነው፡፡

ይህ አዋጅ የጠቅላይ ሚንስትር ዐቢይ አህመድን ወደ ሥልጣን መምጣት ተከትሎ በወቅቱ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ በአሁኑ የፍትሕ ሚኒስቴር ሥር በመመሪያ 1/2018 በተቋቋመው የፍትሕ እና የሕግ ጉዳዮች አማካሪ ጉባኤ ከተረቀቁ ሕጎች መካከል አንዱ ነው፡፡ አዋጁ ከቀዳሚዎቹ መሰል ሕጎች አኳያ ሲታይ አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ በማድረግ ብዙ ተራምዷል፡፡ በርካታ አንቀጾቹ የመራጮች ምዝገባ እና የድምጽ አሰጣጥ ሂደቶች አካል ጉዳተኞችን ያካተቱ መሆን እንደ አለባቸው ይደነግጋሉ፡፡ ከዚህም ባሻገር አካል ጉዳተኞች በፖለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ የሚኖራቸው ሁለንተናዊ ተሳትፎ ከፍ እንዲል የማበረታቻ ስልቶችን አካትቷል፡፡ አካታችነትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎቹን በአጭሩ እንደሚከተለው እንመለከታለን፡፡

### *1. የምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽነት እና አማራጭ የድምጽ መስጫ ዘዴዎች*

"አንቀጽ 15. የምርጫ ጣቢያዎችን ስለማቋቋም"

"1/ የምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ የአካል ጉዳተኞችን ልዩ ሁኔታ ጨምሮ የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በሚወስነው ስፍራ የሚቋቋሙ ሲሆን፤ . . ."

ይህ ድንጋጌ የምርጫ ጣቢያዎችን ተደራሽ ከማድረግ አንጻር ብዙ ተስፋ የተጣለበት ድንጋጌ ነበር። ይሁንና ድንጋጌው የአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ያስቀመጠውን ዝቅተኛ ደረጃ (standard) አያሟላም።

በመጀመሪያ ደረጃ የድንጋጌው ይዘት ስለ ምርጫ ጣቢያዎች መገኛ እንጂ ስለ ጣቢያዎቹ ተደራሽነት አይደለም። የድንጋጌው ዓላማ ምርጫ ጣቢያዎች ሲቋቋሙ ትላልቅ መንገዶች ዳር እንዲሆኑ ወይም ብዙ ሕዝብ የሚጠቀምባቸው እንደ ቀበሌ ያሉ ተቋማት ውስጥ እንዲከፈቱ ለማስቻል ነው። እርግጥ ድንጋጌው ባያስገድድም የምርጫ ጣቢያዎች በባሕርያቸው በመንገድ ዳር እና በተቋማት አካባቢ የሚቋቋሙ ናቸው።

የአካል ጉዳተኞች ትልቁ መሰናክል ግን ወደ ምርጫ ጣቢያ የሚወስደው መንገድ አይደለም። ትልቁ መሰናክል የሚገኘው የጣቢያዎቹ መግቢያ እና የውስጠኛ ክፍል ላይ ነው። የጣቢያዎቹ መግቢያ አንድም ደረጃ የበዛበት፣ ሊፍት የሌለው ፎቅ፣ የተከፈተ ቦይ ያለበት ወይም በሩ ተሽከርካሪ ወንበር የማያስገባ ጠባብ ሊሆን ይችላል። እንደምንም የመግቢያ መሰናክሉ ቢታለፍም ውስጡ ጠባብ፣ በሚስጥር ድምጽ የሚሰጥበት ክፍል ተሽከርካሪ ወንበር የማያስገባ፣ ቢያስገባም ድምጽ ሰጪው ወንበሩን ለማንቀሳቀስ የማያስችል፣ መጻፊያ ጠረጴዛው የተሽከርካሪ ወንበር ተጠቃሚውን ቁመት ያለፈ፣ ወይም መራጭ ከረዳቱ ጋር እንዲገባ እና እንዲመርጥ የማያስችል ጠባብ ሊሆን ይችላል። ይህ ሁሉ መሰናክል በአንቀጽ 15 (1) ታሳቢ አልተደረገም።

“የአካል ጉዳተኞችን ልዩ ሁኔታ ጨምሮ የተለያዩ ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት” የሚለው ሐረግ በራሱ የሕጉን ቁርጠኛ አለመሆን የሚያሳይ ነው። እንደ አንድ የምርጫ ሕግ “ተደራሽ” የሚለውን መርሕ በግልጽ ሊጠቀም በተገባው ነበር። “ተደራሽ” የሚለው ቃል በስምምነቱ ውስጥ ጠንካራ መሰረት ያለው እና በሕግ አተረጓጎም የዳበረ የአካል ጉዳተኞች መብቶች መርሕ ነው። “ግምት ውስጥ በማስገባት” የሚል ሐረግን መጠቀም ግን የሕጉን ጥንካሬ ከማላላቱ ባሻገር ለተለያየ ትርጉም የተጋለጠ ሐረግ ነው።

አንቀጽ 15 (5) . . . ሆስፒታሎች፣ . . . የግል መኖሪያ ቤቶች የምርጫ ምዝገባና የድምፅ መስጫ ሥፍራ በመሆን ሊያገለግሉ አይችሉም።”

ሆስፒታሎች እና የግል መኖሪያ ቤቶች በምርጫ ጣቢያነት እንደማያገለግሉ መደንገጉ እንግዳ ነገር ላይሆን ይችላል። ይሁን እንጂ ሆስፒታሎች እንዲህ ዓይነቱ ክልከላ ሲጣልባቸው ቅድሚያ ታሳቢ መደረግ ያለበት ነገር አለ። በመራጮች ምዝገባ ወቅትም ሆነ በድምጽ መስጫ ቀን በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሕሙማን ሆስፒታሎች ውስጥ ያድራሉ፣ ይሰነብታሉ። አማራጭ የድምጽ መስጫ መንገዶች በምርጫ ሕጉ ስላልተፈቀዱ እነዚህ ሕሙማን ሁሉ ድምጽ የመስጠት እድል የላቸውም።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ መታሰብ ያለባቸው ደግሞ ከመኖሪያ ቤታቸው ርቀው መንቀሳቀስ የማይችሉ ከባድ የአካል ጉዳት ያለባቸው ወገኖች ናቸው። ስምምነቱን በአጸደቁ በርካታ ሀገራት አማራጭ የድምጽ መስጫ መንገዶች ስለሚፈቀዱ እነዚህ አካል ጉዳተኞች የመምረጥ መብታቸውን መጠቀም ይችላሉ። በኢትዮጵያ ይሄ የሚታሰብ አይደለም። በአዋጁ አንቀጽ 5, 20 እና በሌሎችም እንደተደነገገው መመዝገብ ድምጽ መስጠት የሚቻለው በአካል በመገኘት ብቻ ነው። ይህ ዐይነቱ ድንጋጌ በሆስፒታል የተኙ ሕሙማንን እና ከቤታቸው ብዙ ርቀው የማይሄዱ ከባድ የአካል ጉዳት ያለባቸውን ወገኖች ያገለለ ድንጋጌ ነው።

አንቀጽ 17 “ቦርዱ ከምርጫ ክልላቸው ርቀው በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮች፣ ሲቪል ሰራተኞች እና ቤተሰቦቻቸው፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ዜጎች፣ ከመኖሪያ ቀያቸው የተፈናቀሉ ዜጎች እንዲሁም በእስር ቤት የሚገኙ የመምረጥ መብታቸው ያልተገፈፈ ዜጎች . . . ከምርጫው ቀን ቀደም ብለው እንዲመዘገቡና ድምጽ እንዲሰጡ በመወሰን በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው ውስጥ ሊያካትት ይችላል።”

በመሰረቱ ይህ ዐይነቱ የድምጽ አሰጣጥ አማራጭ መንገድ አስቀድሞ ድምጽ መስጠት (early voting) በመባል የሚታወቅ የተለመደ አሰራር ነው። ሌሎች ሀገራት ለአካል ጉዳተኛ መራጮች በስፋት ጥቅም ላይ ያውሉታል። አካል ጉዳተኛው መራጭ የዕለቱ ዕለት ረዳት በማጣት ወይም በሌላ ከአካል ጉዳቱ ጋር በተያያዘ የምርጫ ጣቢያ ድረስ ሄዶ ድምጽ ላይሰጥ ይችላል። በተለይ የህክምና ክትትል የሚያደርግ አካል ጉዳተኛ በምርጫው ዕለት የህክምና ቀጠሮ ሊኖርበት ይችላል። የአካል ጉዳቱ በሚያስከትላቸው መሰል ገደቦች ብዙ አካል ጉዳተኛ መምረጥ እየፈለገ ላይመርጥ የሚችልበት አጋጣሚም ይኖራል። ይህን ታሳቢ በማድረግ አስቀድሞ ድምጽ የመስጠት ዘዴ (early voting) ለአካል ጉዳተኞች እንደ አማራጭ የድምጽ መስጫ ዘዴ ሆኖ በማገልገል የሚታወቅ ቢሆንም በኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ውስጥ ግን አካል ጉዳተኞችን እንዲያገለግል ሆኖ አልተቀረጸም።

አንቀጽ 17 (3) “ቦርዱ በውጭ ሃገር በመኖራቸው ወይም በሌላ ምክንያት በአካባቢያቸው መምረጥ ለማይችሉ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበት ልዩ ሥርዓት የሚዘረጋበትን መንገድ አጥንቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለውሳኔ ያቀርባል።”

በዚህ ድንጋጌ የታሰበው አማራጭ የድምጽ መስጫ መንገድ በሌለበት ድምጽ መስጠት (absentee voting) በመባል የሚታወቀው ነው። ይህ ዐይነቱ አማራጭ ዘዴ እንደ ፖስታ እና እንደ በይነመረብ በመሳሰሉ ዘዴዎች ድምጽ መስጠትን ያስችላል። እንደ ዩናይትድ ስቴትስ በመሳሰሉ ሀገራት አብዛኛው የአካል ጉዳተኛ መራጭ ድምጽ የሚሰጠው በዚሁ ዘዴ ነው። ሆኖም በድንጋጌው ውጭ ሀገር ከሚኖሩት ባሻገር አካል ጉዳተኞች የታሰቡ አይመስሉም። ይህ ድንጋጌ ተፈጻሚ የሚሆነው ቦርዱ አስፈላጊውን ጥናት አድርጎ እና ለፓርላማ አቅርቦ እንዲጸድቅ ከአደረገ በኋላ አፈጻጸም መመሪያ በማውጣት ነው። መመሪያው እስከ አሁን ያልወጣ በመሆኑ ወደፊት ሲወጣ አካል ጉዳተኞችን አካትቶ እንዲረቀቅ ጫና መፍጠር ጥሩ አማራጭ ሊሆን ይችላል።

በመሰረቱ የምርጫ ጣቢያዎች በባሕርያቸው ብዙ ናቸው። በተጨማሪም የምርጫ ጣቢያዎች ጊዜአዊ ናቸው። ይህ ባሕርያቸው በተለይ ለታዳጊ ሀገራት የምርጫ ጣቢያዎችን ሁሉ በአንጼ ተደራሽ የማድረግን ሥራ አዳጋች ያደርገዋል። ከዚህ የምርጫ ጣቢያዎች ባሕርይ የተነሳ ሌሎች ሀገራት አማራጭ የመራጮች መመዝገቢያ እና ድምጽ መስጫ ስልቶችን በመንደፍ እና በምርጫ ሕጎቻቸው ውስጥ በማካተት አካል ጉዳተኛ ዜጎቻቸው ከጉዳት አልባው ዜጎቻቸው ጋር እኩል በሆነ ደረጃ በምርጫ እንዲሳተፉ አስችለዋል። ከእነዚህ አማራጭ የመመዝገቢያ እና ድምጽ የመስጫ ስልቶች መካከል፤ አቅራብ መለስ የድምጽ መስጫ ስልት (curvside voting), በወኪል ድምጽ የመስጠት ስልት (proxy voting)፣ በሌለበት ድምጽ የመስጠት ስልት (absentee voting), ቤት ደረስ ድምጽ የመስጠት ስልት (homebound voting) እና የመሳሰሉት ይገኙበታል። ከእነኝህ እና ከሌሎች በዚህ ጽሑፍ ካልተጠቀሱ አማራጭ የመመዝገቢያ እና ድምጽ የመስጫ ስልቶች መካከል አንዳቸውም በሀገራችን የምርጫ ሕግ አልተካተቱም። ይህ በሆነበት አካል ጉዳተኛ ኢትዮጵያውያን እንደ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የፈለጉትን ለመምረጥ እንዲችሉ ለማድረግ አይቻልም።

*2. ቅድሚያ ስለመስጠት እና ድጋፍ ሰጪ ስለ ማግኘት*

“አንቀጽ 52. ድጋፍ የሚፈልጉ መራጮችን በተመለከተ”

“1/ አካል ጉዳተኞች፣ አረጋዊያን እና ነፍሰ ጡሮች በምዝገባም ሆነ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ቅድሚያ ይሰጣቸዋል።

2/ በምርጫ ድምፅ አሰጣጥ ምልክት ለማድረግና የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ወደ ድምፅ መስጫው ሳጥን ለመክተት እርዳታ የሚያስፈልገው ማንኛውም መራጭ የሚረዳውን ሰው እራሱ የመወሰን መብት አለው፡፡ ምርጫ አስፈጻሚው መራጩ መብቱን አውቆ እንዲጠቀምበት ለማድረግ በተቻለው አቅም ያስረዳዋል፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በድጋፍ ፈላጊው የተመረጠው ሰው ዕድሜ 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ ሆኖ እጩ ወይም የእጩ ተወካይ መሆን የለበትም።”

ይህ ድንጋጌ በብዙ መልኩ የሚደነቅ ድንጋጌ ነው። አንድን አካል ጉዳተኛ ተመዝጋቢ ወይም መራጭ እንዳይሰለፍ ማድረግ እንደየጉዳቱ ዓይነት የተለያየ አንድምታ ይኖረዋል። በአንድ በኩል አካል ጉዳታቸው ለረዥም ሰዓት እንዲቆሙ የማይፈቅድላቸው አካል ጉዳተኞች ብዙ ናቸው። እነዚህን አካል ጉዳተኞች ለብዙ ደቂቃዎች ወይም ሰዓታት ተሰለፉ ማለት አትመዝገቡ ወይም አትምረጡ እንደ ማለት ነው። በሌላ በኩል ቅድሚያ መስጠት ተመዝጋቢውን ወይም መራጩን አካል ጉዳተኛ በቅንነት ለማገዝ የሚነሣሡ በጎ ፈቃደኞችን ያበረታታል። አንድ በጎ ፈቃደኛ ድጋፍ ለማድረግ ከመፍቀዱ ባሻገር ከምታግዘው ሰው ጋር ለሰዓታት ቁመህ ጠብቅ ቢባል ድጋፍ አትስጥ እንደ ማለት ይሆናል።

በንዑስ 2 የተገለጸው ነጻ ፈቃድን መሰረት ያደረገ የድጋፍ አቅርቦት በስምምነቱ አጽንኦት ከሚሰጥባቸው የምርጫ ወቅት ማመቻቸቶች አንዱ ነው። ይሁን እንጂ ይህ ድንጋጌ በብዙ መልኩ ችግር ያለበት ድንጋጌ ሆኖ እናገኘዋለን።

አንደኛ ችግር በንዑስ 3 ረዳቱ እድሜው 18 ዓመት የሞላው ሊሆን ይገባል ማለቱ ነው። በመሰረቱ ረዳቱ እዚህ ላይ እየሠራ ያለው ድጋፍ መስጠትን እንጂ ውል መፈጸምን አይደለም። ረዳቱ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት የዘለለ የመራጩን ተመራጭ መጠቆም ወይም ፖሊሲ መተንተንም አይደለም። መራጭ ረዳቱን የሚፈልገው መብቱን ለመጠቀም በሚያደርገው ጥረት ለሚገጥሙት አካላዊ መሰናክሎች አካላዊ ድጋፍ እንዲሰጠው ነው። ለዚህ ዓይነቱ የተለየ የአእምሮ ብስለትን ለማይጠይቅ ድጋፍ 18 ዓመት የሞላው ብሎ መደንገግ ተገቢነት የለውም።

ሁለተኛ ይህን አካላዊ ድጋፍ ለመስጠት 18 ዓመት የሞላው ብሎ መደንገግ አካል ጉዳተኛ መራጮች የ13-17 ዓመት እድሜ የደረሱ ልጆቻቸውን እንዳይጠቀሙ መከልከል ነው። ድምጽ መስጠት በባሕርይው ሚስጥራዊ ነው። ስለ ሚስጥራዊነት ከተነሣ ደግሞ አንድ ሰው የ30-40 ዓመት እድሜ ከአለው ማኅበራዊ ጓደኛው ይልቅ የ16 እና 17 ዓመት ልጁን ያምናል።

ሶስተኛ ከላይ ለመጠቆም እንደ ሞከርኩት ረዳቱ እየሰጠ ያለው ተግባር ለአንድ ሰው መብት ተግባራዊነት አካላዊ ድጋፍ ማድረግ ነው። ረዳቱ ከመራጭ ጋር በአለው ግንኙነት ራሱን ችሎ እየወሰነ ወይም ውል እየፈጸመ አይደለም። በተቃራኒው ግን በአሠሪና የሠራተኛ ሕጋችን ሕጻናት ከ14 ዓመት እድሜአቸው ጀምሮ ሊቀጠሩ እንደሚችሉ ይደነግጋል። በዚህኛው ሕግ ራሱን ችሎ ውሳኔ እንዲሰጥ ወይም ውል እንዲፈጽም ሥልጣን የተሰጠው ሕፃን በምርጫ ወቅት ውል የሚጠይቀውን አቅም የማይጠይቀውን አካላዊ ድጋፍ እንዳይሰጥ መከልከል የሕጎቻችንን ወጥ አለመሆን ከማሳየት በስተቀር አሳማኝ ሕጋዊ አመክንዮ የለውም።

አራተኛ በድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 14/ 2013 አንቀጽ 26 (4) እንደተገለጸው አንድ ድጋፍ ሰጪ ድጋፍ መስጠት የሚችለው ለአንድ መራጭ ብቻ ነው። ይህም በራሱ ከብዙ ሀገራት መሰል ድንጋጌዎች የሚቃረን እና ብዙ ያልተጤነ ድንጋጌ ነው። በዚህ ድንጋጌ መሰረት ሁለት ባልና ሚስት ዓይነ ስውራን መራጮች የ20 ዓመት እድሜ ካለው ልጃቸው ይልቅ ሌላ ሦስተኛ ወገንን እንዲጠቀሙ ይገደዳሉ ። ሚስጥርን ከማካፈል፣ እምነትን ከማሳደር፣ በድጋፉ ምቾት ከማግኘት፣ የፈለጉትን ከማዘዝ እና ከመሳሰሉት አንጻር ለአካል ጉዳተኛ መራጮች እንደ ልጆቻቸው የሚሆንላቸው ላይኖር ይችላል። ሆኖም በዚህ ድንጋጌ መሰረት የአንድ የቤተሰብ አባላት የሆኑ አካል ጉዳተኛ መራጮች እኅታቸውን፣ ወንድማቸውን፣ ልጃቸውን ወይም የቅርብ የጋራ ጓደኛቸውን ድጋፍ ማግኘት እና መምረጥ አይችሉም።

አምስተኛ በመራጮች ምዝገባ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 6/2013 አንቀጽ 22 (4) ለምዝገባ የሄደ አንድ አካል ጉዳተኛ ድጋፍ ቢያስፈልገው የምርጫ መዝገብ ሹሙ ለምዝገባ ከመጡ ተመዝጋቢዎች መካከል ፈቃደኛ የሆነ ፈልጎ አካል ጉዳተኛው መራጭ ድጋፍ እንዲያገኝ ማድረግ አለበት ይላል። ይሄ ድንጋጌ የመራጩን መብት በሦስተኛ ወገን ፈቃደኝነት ላይ እንዲመሰረት ያደረገ ድንጋጌ ነው። እንዲህ ዓይነቱ የመብት አፈጻጸም በየትኛውም የሰብአዊ መብት አመክንዮ በሕግ ፊት ተቀባይነት የለውም። በመጀመሪያ ደረጃ አካል ጉዳተኛው መራጭ ድጋፉን በሚፈልግበት ወቅት ሌላ ተመዝጋቢ ሰው ላይኖር ይችላል። ሁለተኛ ሌላ ተመዝጋቢ ቢኖርም በተለያየ ምክንያት ድጋፍ ለማድረግ ፈቃደኛ ላይሆን ይችላል። ሦስተኛ በዚህ መንገድ የተገኘ ድጋፍ ምንጩ መብት ሳይሆን ችሮታ ነውና ለተቀባዩ የሥነ ልቦና ቁስል ማስከተሉ አይቀሬ ነው። አራተኛ በድምጽ መስጠት ወቅት ድጋፍ ፈላጊው የራሱን ድጋፍ ሰጪ ካላመጣ የምርጫ አስፈጻሚ ሹሙ ድጋፍ የማድረግ ግዴታ እንደ አለበት በድምፅ አሰጣጥ፣ ቆጠራና ውጤት አገላለፅ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 14/ 2013 አንቀጽ 26 ተደንግጓል። በድምጽ መስጫ ቀን ድጋፍ የሚሰጠው ሹም በምዝገባ ወቅት ለምን ተመሳሳይ ድጋፍ እንደማያደርግ ምንም አመክንዮ ሊሰጠው አይችልም።

### *3. አእምሮአዊ አካል ጉዳትን መሰረት ያደረገ የመምረጥና የመመረጥ መብት ክልከላ*

በአንቀጽ 18, 28, 31-33 እና በሌሎች አንቀጾች የአእምሮ ሕመምተኛ የመምረጥም ሆነ የመመረጥ መብት እንደሌለው ተደንግጓል። እንዲህ ዐይነቱ ክልከላ ስምምነቱን ከመቃረኑ ባሻገር ብዙ የትርጉም እና የአፈጻጸም ችግሮችን ያስከትላል።

በመጀመሪያ ደረጃ የአእምሮ ሕመምተኛ ማነው? ይህ ጥያቄ በረቂቁ በደንብ የታሰበበት አይመስልም። በፍትሐ ብሔር ሕጉ አንቀጽ 339 (1) በተቀመጠው መሰረት ከሆነ የአእምሮ ሕመም ያለባቸው ሰዎች የአእምሮ እድገት ውሱንነት ያለባቸውን ወገኖች አይጨምርም። የፍትሐ ብሔር ሕጉ በቆየ አገላለጹ "የአእምሮ ጉድለት ያለበት ሰው (insane person) "በተፈጥሮ ዕውቀቱ ያልተስተካከለ በመሆኑ፤ ወይም በአእምሮ መናወጥ ወይም በእርጅና ምክንያት የሚሠራው ሥራ የሚያደርሰውን ለማወቅ የማይችል ነው" በማለት ይደነግጋል። "በአእምሮ መናወጥ" የሚለው ሐረግ የአእምሮ ሕመም ለማለት ስለ መሆኑ "mental disease" ከሚለው የሐረጉ የእንግሊዘኛ ቅጂ ለማየት ይቻላል። በዚህ መሰረት የግልጽ ትርጓሜ (textualism) ስልትን ከተጠቀምን በምርጫ ሕጉ እንዳይመርጡ እና እንዳይመረጡ የተከለከሉት የአእምሮ ሕሙማን እንጂ የአእምሮ እድገት ውሱንነት ያለባቸው ወገኖች አይደሉም ብሎ ለመከራከር ይቻላል።

ይሁንና የሕግ አውጪውን ሀሳብ ትርጓሜ (intentionalism) ስልትን ተጠቅመን ከተረጎምን ውጤቱ የተለየ ይሆናል። በዚህ የትርጓሜ ስልት የሕጉን ትክክለኛ መንፈስ ለማወቅ የሕጉን ዳራ ታሪክ መመርመር እና የሕግ አውጪውን ሀሳብ ማግኘት ያስፈልጋል። ለዚህ አተረጓጎም ሁነኛ መፍትሄ የሚሆነው ደግሞ የምርጫ ሕጉ ሲረቀቅ የተዘጋጀው የሕጉ መግለጫ

(explanatory note) ነው። በመግለጫው የአእምሮ ሕመም ያለባቸው የሚለው አገላለጽ የአእምሮ እድገት ውሱንነትን እንደማይጨምር የተባለ ነገር የለም። ሆኖም የትኛንውም አተረጓጎም ብንከተል የሕጉን ከስምምነቱ መጣረስ አያስቀረውም።

ስምምነቱን ያጸደቁ እና በአእምሮአዊ አካል ጉዳተኛ ዜጎቻቸው ላይ የመምረጥ እና የመመረጥ ገደብን ያላስቀመጡ ሀገራት በወኪል ድምጽ የመስጠት ዘዴን (proxy voting) ይጠቀማሉ። በዚህ አሠራር በራሳቸው ሄደው ለመምረጥ የሚቸገሩ አካል ጉዳተኞች በወኪሎቻቸው አማካኝነት መምረጥ እንዲችሉ ለማድረግ ነው። በተለይ ጽኑ የአእምሮአዊ አካል ጉዳት ያለባቸው መራጮች ይህንን ዘዴ በስፋት ይጠቀማሉ። በዚህ አሠራር የትኛውም የአካል ጉዳት የመምረጥ መብትን ለመንፈግ ምክንያት አይሆንም ከሚለው የስምምነቱ አቋም ጋር መጣጣም ይቻላል።

### *4. አካል ጉዳተኝነትን የሚገልጽ አምድ ስለመካተቱ*

በአንቀጽ 22 እንደተደነገገው የመራጮች መዝገብ ሊኖሩት ከሚገባው አምዶች መካከል ተመዝጋቢው አካል ጉዳተኛ ከሆነ የጉዳት ዐይነቱ የሚመዘገብበት አምድ ይገኝበታል። ይህ በሀገራችን ከሚታየው አካል ጉዳተኝነትን በተመለከተ የዳታ አያያዝ ችግር አኳያ አድናቆት የሚቸረው እርምጃ ነው። ሆኖም በምርጫ ጣቢያዎች ተደራሽ አለመሆን እና በአጋጣሚ ተደራሽ ቢሆኑም እንኳ በምርጫ አስፈጻሚዎች የግንዛቤ ችግር ምክንያት የአካል ጉዳት ዐይነት የሚመዘገብበትን አምድ አይጠቀሙበትም። ምርጫ ቦርድም ቢሆን በየጊዜው በሚሰጣቸው መግለጫዎች ይህን ያህል ሴት እና ይህን ያህል ወንድ ተመዘገበ ከማለት የዘለለ ይህን ያህል አካል ጉዳተኛ መራጭ ተመዘገበ ሲል አይደመጥም።

### *5. ገላጭ ውክልናን ስለማበረታታት*

በሌላ በኩል በአንቀጽ 100 እንደተቀመጠው ፓርቲዎች ከመንግስት ለሚያገኙት የገንዘብ ድጋፍ ያላቸው የአካል ጉዳተኛ አባላት ብዛት፣ ያቀረቡት የአካል ጉዳተኛ እጩ ተወዳዳሪ ብዛት እና በአመራር ውስጥ ያሳተፉት የአካል ጉዳተኛ አመራር ብዛት እንደ መስፈርት መወሰዱ ድንቅ እርምጃ ነው። ይህ ዐይነቱ ማበረታቻ በምርጫ ካልሆነ በስተቀር የፓርላማ ውክልናን ለማግኘት ለማይቻለው የእኛ ሀገር የአካል ጉዳተኛ ማኅበረሰብ ትልቅ አንድምታ ይኖረዋል።

አካል ጉዳተኛ ኢትዮጵያውያን በፓርላማ እንዲወከሉ እና ድምጻቸውን እንዲያሰሙ የሚያስችል ሕገ መንግሥታዊ መሰረት የለም። በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 53 (3) ከ20 ያላነሰ የፓርላማ መቀመጫ ለአናሳ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች እንደሚሰጥ ቢደነገግም ለአካል ጉዳተኞች የሚሠራ አይሆንም። አካል ጉዳተኛ ኢትዮጵያውያን በቁጥር ትልቁን የአናሳ ቡድን ቢይዙም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 39/5/ በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ብሔረሰብ እና ሕዝብ አይደሉም።

አካል ጉዳተኛ ኢትዮጵያውያን ተያያዥ በሆነ ግዛት አይኖሩም። አካል ጉዳት በዘር፣ በአካባቢ፣ ወዘተ የሚወሰን ባለመሆኑ በየትኛውም ማኅበረሰብ እና አካባቢ የሚደርስ ክስተት ነው። አሁን ያለው የሀገራችን የአብላጫ ድምጽ የምርጫ ስርዐት (first past the post) ደግሞ ተያያዥ በሆነ ግዛት እንጂ በተለያየ ግዛት እና ማኅበረሰብ ውስጥ ተሰባጥሮ ለሚኖር አናሳ ቡድን አይሆንም። እንዲህ ያለ የምርጫ ስርዐት የሚከተሉ ሀገራት የአካል ጉዳተኛ ዜጎቻቸው በፓርላማ እንዲወከሉ ለማስቻል የሕግ፣ የምርጫ ወይም የፓርቲ ኮታ ስርዐትን ይጠቀማሉ። ይህም ማለት ፓርላማ የገቡ ፓርቲዎች በፓርላማው ውስጥ አካል ጉዳተኞችን ለሚወክሉ መቀመጫዎች ኢቀጥተኛ በሆነ መንገድ አካል ጉዳተኞችን የሚወክሉ ተሿሚዎችን ይሾማሉ፤ ወይም በሕገ መንግሥታቸው የተወሰነ ቁጥር ያለውን መቀመጫ ለአካል ጉዳተኞች ሪዘርቭ ያደርጋሉ፤ ወይም እያንዳንዱ ፓርቲ ከሚያቀርባቸው እጩዎች መካከል የተወሰኑት አካል ጉዳተኞች ብቻ እንዲሆኑ ያስገድዳሉ፤ ማለት ነው። በእኛ ሀገር ግን የፓርላማ መቀመጫ የሚያዘው በሕገ መንግሥቱ መሰረት በቀጥተኛ ምርጫ ብቻ በመሆኑም በእነዚህ ስልቶች አካል ጉዳተኛ ኢትዮጵያውያን በፓርላማ እንዲወከሉ ለማድረግ አይቻልም።

ከምርጫ ስርዐት አኳያ ሲመዘን ደግሞ በተለያየ ግዛት እና ማኅበረሰብ ውስጥ ተሰባጥሮ የሚኖር ማንኛውም አናሳ ቡድን በፓርላማ እንዲወከል የሚያስችለው የምርጫ ስርዐት የተመጣጣኝ ውክልና (proportional representation) የምርጫ ስርዐት እንጂ የአብላጫ ድምጽ (first past post) የምርጫ ስርዐት አይደለም። በእኛ ሀገር ተፈጻሚ የሚሆነው የምርጫ ስርዐት ደግሞ የአብላጫ ድምጽ ስርዐት በመሆኑ በተለያየ አካባቢ እና ማኅበረሰብ ውስጥ የሚኖሩት አካል ጉዳተኛ ኢትዮጵያውያን በግዛት የተበታተነ ድምጻቸውን በማሰባሰብ ተወካዮቻቸውን መርጠው ወደፓርላማ ለማስገባት አያስችላቸውም።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ በአንቀጽ 31 እና 32 እጩ አካል ጉዳተኛ ተወዳዳሪ ከጉዳት አልባው ተወዳዳሪ ያነሰ የድጋፍ ፊርማ እንዲያሰባስብ አውንታዊ ድጋፍ (affirmative action) መደንገጉ አካል ጉዳት በራሱ ከሚጠይቀው ተጨማሪ የገንዘብ፣ የጉልበት እና የጊዜ ወጭ አንጻር መልካም ነው። ሆኖም እጩ የግል አካል ጉዳተኛ ተወዳዳሪ ከመንግሥት በኩል የገንዘብ ድጋፍ የማይደረግለት በመሆኑ ከጉዳት አልባው የግል እጩ ተወዳዳሪ አንጻር ድካሙ የበዛ ይሆናል። እጩ አካል ጉዳተኛን ካቀረቡ ፓርቲዎች በበለጠ በግሉ ለሚወዳደር አካል ጉዳተኛ ልዩ የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

## 4. እንደ ማጠቃለያ

የምርጫ ሕጉ አካል ጉዳተኞችን ከማሰቡ አንጻር ሊወደስ ቢገባም ከአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት ጋር ለመጣጣም እና አካታች ምርጫን ለማድረግ ግን እጅግ በርካታ ክፍተቶች ያሉበት እና ብዙ ሥራ የቀረው ሆኖ ይታያል። ስለ ሆነም አዋጁን እና መመሪያዎቹን በማሻሻል ከአካል ጉዳተኞች መብቶች ስምምነት እንዲጣጣም ማድረግ ያስፈልጋል። ገና ሊወጡ የታሰቡ መመሪያዎች ላይ አስፈላጊውን ጫና በመፍጠር እውነተኛ አካታች መመሪያ ሆነው እንዲወጡ ማድረግም ያስፈልጋል። የፖለቲካ ፓርቲዎች እጩ አካል ጉዳተኞችን ከማቅረብ ባሻገር የአካል ጉዳተኞች ሊግን እንዲያቋቁሙ ሊሠራ ይገባል። እንዲህ ካልሆነ በትክክል አካል ጉዳተኛውን ማኅበረሰብ የሚወክል አካል ጉዳተኛን የማግኘት እድላቸው የጠበበ ይሆናል። እጩ የግል አካል ጉዳተኛ ተወዳዳሪዎች ከመንግሥት በኩል የገንዘብ ድጋፍ ሊደረግላቸው ያስፈልጋል።